# የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 ማሻሻያ አጭር ማብራሪያ

## 1/ መግቢያ

የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 በ 2006 ዓ.ም በህዘብ ተወካዮች ምክርቤት መታወጁ ይታወሳል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት እያካሄደች ካለችው ዘርፈብዙ የልማት ስራ አኳያ እና በቀጣዮቹ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ጊዜያት ውስጥ ኢኮኖሚው ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚያደርገው የሽግግር ሂደት ቁልፍ ከሆኑት ግብዓቶች ውስጥ አንዱ ኢነርጂ በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የግል ዘርፉን በዚህ መስክ በበቂ ሁኔታ ለማሳተፍ እንዲቻል የሕግ ማዕቀፉን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

በስራ ላይ ያለውን የኢነርጂ አዋጅ ወደ ዘርፉ የሚገቡትን አልሚዎች ፈጥነው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም በሴክተሩ ውስጥ በልማት የሚሳተፉ አካላት የልማት ሥራው የሚወስደውን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የሕግ ማዕቀፉ ግልጽና ኢንቨስትመንትን ሳቢ እንዲሁም የማያሻማ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ የነባሩ አዋጅ የተወሰኑ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

## 2/ የኢነርጂ አዋጅ 810/2006ን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት

የታዳሽ የሃይል ማመንጫዎችን በመጠቀም የኤሌክትሪክ ሀይል በማመንጨት ለሚሳተፉ የግሉዘርፍ አልሚዎች የፈቃድ አሰጣጡ የሚሰጠውን የጊዜ ገደብ እንደ ፕሮጀክቶች ዓይነት በቂ ሊባል የሚችል ጊዜ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተወሰኑ አንቀጾችን ማስካከሉ አሲፈላጊ ሆኖ ተገኝቶዋል፡፡

የባለፈቃድ ግዴታዎች በሚል ርዕስ "ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ፣ በማከፋፈልና፣ በመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር በመላክ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ባለፍቃድ ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ ስራ እንዲጀምር ተብሎ የተደነገገው ጊዜው አጭርና አልሚዎችን የማያበረታታ በመሆኑ መሻሻል ያስፈልገዋል፡፡



www.chilot.me

3/ <u>በማሻሻው ውስጥ ተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች</u>

**አንቀጽ2/9/** የኤሌክትሪክ ሥራ ማለት የኤሌክትሪክ ዲዛይን፣ ኢንስታሌሽን፣ ጥገና፣ ፍተሻ፣ መቆጣጠር፣ ተቋራጭነት ወይም ማማከር፣የኤሌክትሮ መካኒካል ስራ ወይም ማንኛውም ሌላ ኤሌክትክ ነክ የንግድ ስራ ነው።" ተብሎ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን መጨረሻ መደምደሚያው ማንኛውም ሌላ ኤሌክትሪክ ነክ የንግድ ሥራ ነው መባሉ ትርጉሙን ያዛባው ስለሆነ "ንግድ" የሚለውን ቃል ብቻ በማውጣት ትክክለኛውን ትርጉም እንዲሰጥ "ማንኛውም ሌላ የኤሌክትሪክ ሥራ" በሚል እንዲሻሻል፤

**የአዋጁ አንቀጽ** 10/3/- የባለፈቃድ ግዴታዎች በሚል ርዕስ ንኡስ አንቀጽ (3) በነባሩ አዋጅ "ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ፣ በማከፋፈልና፣ በመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር በመላክ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ባለፍቃድ ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ ስራውን መጀመርና ስራውን ስለመጀመሩም ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት" የሚል ሲሆን

የአስራ ሁለት ወራት የጊዜ ገደብ ማስቀመጡ ግልጽነትና ተጠያቂነትን እንዲኖር ለማድረግ የተቀመጠ ድንጋጌ ቢሆንም በመጀመሪያው ማብራሪያ ላይ የጊዜ ገደቡ ሲቀመጥ በፈቃዱ ላይ እንዲገለጽ የቀረበውን ሀሳብ በማስተካከል በአስራ ሁለት ወራት ኮንስትራክሽኑን ገንብቶ የኃይል ማምረት ወይም አቅርቦት መስጠት እችላለሁ ብለው ግዴታ ውስጥ ለመግባት የማይስማሙበትና በዚህ ጊዜ ውስጥ ይህን ማድረግ የማይቻል በመሆኑ አልሚዎችና ባለሀብቶችን የማያበረታታ እና አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች የሆኑ የውጪ ሀገር ሰዎች አስተያየታቸውን አካፍለውናል።

በመሆኑም ወደፊት አልሚዎች ሲመጡ የመጀመሪያው ችግር የሚሆነው የአዋጁ አንቀጽ 10(3) የተቀመጠው ድንጋጌ ለተወሰኑ የኢነርጂ ዘርፎች ለምሳሌ ጂኦተርማል፣ የውኃ ሀይል ማመንጫ እና ለመሳሰሉ በአዋጁ ላይ የተቀመጠው የአስራ ሁለት ወራት ገደብ በጣም አነስተኛ ሆኖ ስለተገኘ እና የጊዜ ገደቡ ለተለያዩ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችና ለተለያዩ የማመንጫ ሀይል መጠን የተለያየ ስለሆነና የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ ለምሳሌ ያህል የኢንዶኔዥያ፣ ብራዚል ወ.ዘ.ተ. ሐገሮች በአብዛኛው ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ መሆኑ ልምድ ተወስዷል።

ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ በወሰዱ በ12 ወራት ውስጥ ፈቃድ የወሰዱበትን የኤሌክትሪክ ሥራ ማለት የማመንጨት ሥራ መጀመር እንዳለባቸው የተቀመጠው የጊዜ ገደብ አንዳንድ ኢንቨስትመንቶችን ከቴክኖሎጂው ባሕሪይ አቅምና ከሚጠይቀው ሥራ አንጻር በሁሉም



www.chilot.me

አይነት የዘርፉ ኢንቨስትመንት ላይ ተግባራዊ ማድረግ አዳጋች ነው፡፡ በተጨማሪም በኤሌክትሪክ አቅርቦት ላይ የሚሰሩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ሰፊ ጊዜ ሲወስዱ ይታያል፡፡ ባለሀብቶችም የሚሰጣቸው የኤሌክትሪክ ሥራ ፈቃድ ተገቢውን ጊዜ ሰጥቶ ሊያሰራቸው የማይችል ከሆነ መዋዕለንዋይ እንዲያፈሱ ስለማያበረታታ አንቀጹን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

በዚህም መሰረት የተሰጠው የአስራ ሁለት ወራት የጊዜ ገደብ ላይ የአንድ ጊዜ እድሳት ቢጨመርበት ሁለት ዓመት ብቻ ይሆንና አሁንም የጊዜ እጥረትን ሊፈጥር ስለሚችል በኤሌክትሪክ ማመንጫው በኩል ሰፊ የግባንታ ጊዜ የሚጠይቁትን የቴክኖሎጂ ዓይነቶች ማለትም ጂኦተርማልን የውኃ ኃይልን ሊሰጥ የሚችል የጊዜ ገደብ አምስት ዓመት ሆኖ አዲስ አንቀጽ እንዲጨመር እንዲሁም ሌላ ተጨማሪ ንዑስ አንቀጽ በፀሀይ፣ለንፋስ ለባዮ ማስ፣የድንጋይ ከሰል ለተፈጥሮ ጋዝ ለሚሰሩ የማመንጫ ቴክኖሎጂዎች የሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ እና እንደ ፈቃድ ዓይነቱ እና እንደሚወስደው ጊዜ መጠን በፈቃድ ውል ስምምነት መሰረት ይህንኑ ጊዜ ማሳጠር ወይም በዕድሳት መልክ ተጨማሪ ጊዜ መስጠት እንደሚቻል ታሳቢ ተደርጎ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

ማዕድናቱን ለመፈለግና ለማግኘት የሚያስፈልገው ጊዜ በዚህ ማዕቀፍ ያልተካተተና በስራ ላይ ባለው የማዕድን አዋጅ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

በዚህ ማሻሻያ መሠረት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ከአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (5)፣ (6) እና (7) ጋር አብረው የሚናበቡ ሲሆን ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራ ያልጀመረ ባለፈቃድ ፈቃዱ በአንቀጽ 8 መሠረት ሊታደስ ወይም ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታ በግልጽ እንዲመላከት ተደርጓል፡፡

ኤልክትሪክ የማስተላለፍ፣የማከፋፈልና የመሸጥ ስራዎች ለግል ባለሃብት የሚሰጡ ሳይሆኑ የመንግስት የስራ ድርሻዎች ናቸው፡፡የግል ባለሃብቶች ኤሌክትሪክ ካመነጩ በኂላ ለመንግስት ይሸጣሉ ማለት ነው፡፡ይህንና ሌሎችንም የአዋጁን ድንጋጌዎች አፈፃፀም በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በማውጣት ዝርዝር አሰራሮችን ያስቀምጣል፡፡

በሌላ በኩል ኦፍ ግሪድን በተመለከተ በአገሪቱ የኢንቨስትመንት ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል



www.chilot.me

4/. <u>ማጠቃለያ</u>

በዚህም መሰረት የተሰጠው የአስራ ሁለት ወራት የጊዜ ገደብ ላይ የአንድ ጊዜ እድሳት ቢጨመርበት ሁለት ዓመት ብቻ ይሆንና አሁንም የጊዜ እጥረትን ሊፈጥር ስለሚችል በኤሌክትሪክ ማመንጫው በኩል ሰፊ የግባንታ ጊዜ የሚጠይቁ ቴክኖሎጂ ዓይነቶች ማለትም ጂኦተርማልና የውኃ ሀይልን ሊሰጥ የሚችል የጊዜ ገደብ አምስት ዓመት ሆኖ አዲስ አንቀጽ እንዲጨመር፤ እንዲሁም ሌላ ተጨማሪ ንዑስ አንቀጽ በፀሀይ፣ በንፋስ በባዮማስ፣ በድንጋይ ከሰል በተፈጥሮጋዝ ወ.ዘ.ተ. ለሚሰሩ የማመንጫ ቴክኖሎጂዎች የሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ እንዲሆን ከማዕድን ሥራዎች ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሞክሮ በማየት ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ባለፈቃድ ሥራ ያልጀመረው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ማመልከቻ አቅርቦ ባለስልጣኑም ይህንኑ ካረጋገጠ ፈቃዱን ለሁለት ጊዜ ብቻ በየዓመቱ ሊታደስ እንደሚችል እና ባለፈቃድ ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ሥራውን ሳይጀምር እና በአዋጁ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ሳያከብር ሁለት ዓመት ካለፈው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈቃዱ እንደሚሰረዝ እንዲሁም በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመሩን ለባለስልጣኑ በሪፖርት ካሳወቀ፣ እንደሁኔታው ባለሥልጣኑ ክትትል አድርጎ ማረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፈቃድ ዘመኑ ባለፈቃዱ ሥራ ስለመጀመሩ ሪፖርት ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ መቆጠር እንደሚጀምር ተደረጎ አዳዲስ ማሻሻያ ሀሳቦች እንዲካተቱ ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

በመሆኑም የተከበረውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕጉን መሻሻል አስፈላጊነት ተመልክቶ ውሳኔ እንዲሰጥና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ ወደሥራ መግባት እንድንችል ይህ ማሻሻያ ቀርቧል፡፡



www.chilot.me